15 ኛ ዓመትአዋጅ ቁጥር 73
አሶሳ ነሐሴ 2000

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት**
**ልሣነ- ሕግ ጋዜጣ**

**በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት**
**ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ**

*ማውጫ*
*አዋጅ ቁጥር 73/2000 ዓ.ም*

# በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የብሄረሰቦች ምክር ቤቶችንና ጽህፈት ቤቶችን ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸዉና የዉስጥ አሰራራቸዉን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

## መግቢያ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ብሄር ብሄረሰቦች በኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ህገ መንግስት ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ያላቸዉ በመሆኑና የራሳቸዉን ብሄራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ቅርስንና ታሪካቸዉን የመንከባከብና የማበልጸግ እንዲሁም እያንዳንዱ ብሄረሰብ ቋንቋዉን የመጠበቅ፣ የማሳደግ፣ባህሉን የመግለጽ የማዳበርና የማስፋፋት መብት በተሸሻለዉ የክልሉ ህገ መንግስት የተረጋገጠ በመሆኑ፣

የክልሉ ብሄረሰቦች በራሳቸዉ መልከአ ምድራዊ ክልል ዉስጥ የራሳቸዉን ጉዳይ በራሳቸዉ የመጨረስ፣በሰፈሩበት መልከአ ምድር ራሳቸዉን የሚያስተዳድሩበት መንግስታዊ ተቋማት የማቋቋም መብትን ተግባራዊ ማድረግ በመታመኑ፣

እንዲሁም የብሄረሰብ አስተዳደር መደበኛ የመንግስት የተዋረድ የአስተዳደር እርከን በመሆኑና የየብሄረሰቡ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት፣ አደረጃጀት፣፣ስልጣንና ተግባር እንዲሁም የዉስጥ አሰራርን በዝርዝር ህግ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት በተሸሻለዉ የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 49(3) 1 መሰረት የሚከተለዉ ታዉጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ ‹‹በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የብሔረሰቦች ምክር ቤቶች እና ጽህፈት ቤቶች አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውንና የዉስጥ አሰራር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 73/2000›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

3. የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

‹‹ብሔረሰብ›› ማለት በተሻሻለው ሕገ መንግሥት አንቀጽ 2 መሠረት የክልሉ ባለቤት ናቸው ተብሎ እውቅና የተሰጣቸው በርታ፣

1. ጉሙዝ፣ ሺናሻ፣ ማኦ እና ኮሞ ብሄረሰቦች ናቸው።

2. ‹‹የብሔረሰብ ምክር ቤት›› ማለት ለክልሉ ምክር ቤት አባልነት የተመረጡትን የብሄረሰብ አባላት ጨምሮ በውስጡ ከታቀፉት የወረዳ ምክር ቤቶች በልዩ ሁኔታ የሚመረጡ አባላት ያሉበት ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ሆኖ የተቋቋመ ምክር ቤት ነው።

3. ‹‹ሌሎች ሕዝቦች›› ማለት በክልሉ ውስጥ ለረጅም ዘመናት በተለያዩ መልኮችና ደረጃዎች ከክልሉ ብሔረሰቦች ጋር ተሳስሮ የቆዩና ከብሔረሰቦቹ ጋር በመፈቃቀድ ክልሉን አቋቁመው በጋራ ባፈሩት እሴቶች ላይ በመመስረትና በማጉልበት ክልሉን ወደ ተሻለ የእድገት ጉዳና ለመምራት ፅኑ እምነት ያላቸው ሕዝቦች ናቸው።

4. ‹‹ምክር ቤቱ›› ማለት የየብሄረሰቡ ምክር ቤት ነው።

5. ‹‹የብሔረሰብ አስተዳደር እርከን›› ማለት የብሔረሰብ ምክር ቤት፣ የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት እና የብሔረሰብ አስተዳደር የዳኝነት አካላት ኖሮት ከክልሉ አስተዳደር እርከን ቀጥሎ የተቋቋመ የአስተዳደር እርከን ነው።

6. ‹‹ሕገ መንግሥት›› ማለት የተሻሻለው የ1995 ዓ.ም. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ነው።

7. ‹‹ኮሚቴ›› ማለት አንድን ጉዳይ ለማከናወን እንደ ሁኔታው በብሔሰብ ምክር ቤቱ የሚቋቋም ቋሚ፣ ንዑስ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴ ነው።

8. ‹‹ቋሚ ኮሚቴ›› ማለት በሕግ ተወስኖ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር ዙሪያ የምክር ቤቱን ተግባር ለማቀላጠፍ ሲባል በብሔረሰብ ምክር ቤት የሚቋቋምና በቋሚት የሚሠራ ኮሚቴ ነው።

9. ‹‹ንዑስ ኮሚቴ›› ማለት ማንኛውም የምክር ቤቱ ኮሚቴ ለሥራው ቅልጥፍና እንዲያግዘው ከራሱ አባላት መካከል መርጦ የሚያቋቁመው ኮሚቴ ነው።

10. ‹‹ጊዜያዊ ኮሚቴ›› ማለት አስቸኳይ ሁኔታ ሲፈጠር ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና ተግባሩ በሚመለከተው ኮሚቴ ወይም ኮሚቴዎች ሊከናወን የማይቻል ነው ተብሎ የታመነ ጉዳይ ለማከናወን በምክር ቤቱ የሚቋቋም ኮሚቴ ነው፡ ፡

11. ‹‹የብሔረሰብ ነክ ጉዳዮች ›› ማለት በፌዴራል ስርአቱ ብሄር ብሄረሰቦች በቋንቋ ለመናገር ለመጻፍ፣ቋንቋዉን

ለማሳደግ፣ ለመጠበቅ፣ለመግለጽ፣ ለማዳበርና ለማስፋፋት፣እንዲሁም ታሪኩን ለመንከብከብ ያለዉን መብትና በፌዴራልና በክልሉ ህገ መንግስት ለብሔረሰቦች የተሰጠዉን መብት ያካትታል፡፡

12. ‹‹የኮሚቴ አመራሮች›› ማለት አንድን የምክር ቤት ኮሚቴ በበላይነት የሚመሩ ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ናቸው፡፡

13. ‹‹አፈ ጉባኤ›› ማለት የየብሔረሰብ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ነው፡፡

14. ‹ጽህፈት ቤት››ማለት የየብሔረሰብ ምክር ቤት እና የአፈ ጉባኤ ጽህፈት ቤት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

### የምክር ቤቱ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራትን ስለመወሰንና እና ጽህፈት ቤቱን ስለማቋቋም፣

### 4. ስለማደራጀትና ማቋቋም

1. እያንዳንዱ ብሔረሰብ በሚኖርበት አካባቢ ራሱን በራሱ የሚስተዳድርበት አምስት የብሔረሰብ ምክር ቤቶች በዚህ አዋጅ የተደራጁ ሲሆን የየብሄረሰብ ምክር ቤት ጽህፈት ቤቶች (ከዚህ በኋላ ጽህፈት ቤት) እየተባለ የሚጠራ ህጋዊ ሰዉነት ያለዉ አካል በአዋጅ ቁጥር 32/1995 አንቀጽ(4) እና በዚህ አዋጅ መሰረት ተቋቁሟል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተደራጁት የክልሉ የብሔረሰቦች ምክር ቤቶች፤
   ሀ. የበርታ ብሔረሰብ ምክር ቤት፣
   ለ. የጉሙዝ ብሔረሰብ ምክር ቤት፣
   ሐ. የሺናሻ ብሔረሰብ ምክር ቤት፣
   መ. የማኦ ብሔረሰብ ምክር ቤት፣
   ሠ. የኮሞ ብሔረሰብ ምክር ቤት ናቸዉ፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ሥር የተደራጁ ምክር ቤቶች ራሳቸዉን በራሳቸዉ የሚያስተዳድሩበት ማዕከል ወይም የምክር ቤቱ መቀመጫ ከተማን በተመለከተ በየብሄረሰቡ ምክር ቤት የሚወሰን ይሆናል፡፡

4. የብሄረሰቡ የአስተዳደር እርከን መደበኛ መንግስታዊ ተግባራትንና የአስተዳደር ስራዎችን ለማከናወን የየራሱ የአስተዳደር ወሰን የሚኖረዉ ሲሆን ብሄረሰቦቹ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 39 የተረጋገጠላቸውን ብሄረሰብ ነክ መብቶችንና ጥቅሞችን ለማስከበርና ለማስጠበቅ በክልሉ ዉስጥ ድንበር የለሽ ሆኖ ተቋቋሚል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) የተመለከቱት ምክር ቤቶች ቢኖሩም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 39 (7) በተደነገገዉ መሰረት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸዉ፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ

ያላቸዉ የጋራ ወይም የተዛመደ ህልዉና አለን ብለዉ የሚያምኑና የስነ ልቦና አንድነት ያላቸዉና በአብዛኛዉ በተያያዘ መልከአምድር የሚኖሩ ብሄረሰቦች በስምምነት የብሄረሰብ ምክር ቤቱንም ሆነ የአስተዳደር እርከኑን በጋራ ሊያደራጁ ይችላሉ፡፡ ስለአፈጻጸሙ በጋራ በሚያወጡት መመሪያ ይወሰናል፡፡

6. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም የየብሄረሰቡ የአስተዳደር እርከን ስያሜ በየብሄረሰቡ ምክር ቤት ሊወሰን ይችላል፡፡

7. ከላይ በንኡስ አንቀጽ 2 ስር በተደራጁት ምክር ቤቶች ዉስጥ የሌሎች ህዝቦች ዉክልና በህገ መንግስቱ አንቀጽ 45 (3) መሰረት በልዩ ሁኔታ ይታያል፡፡

## 5. ስለ ብሄረሰብ ምክር ቤትና የብሄረሰብ አስተዳደር ምክር

1 እያንዳንዱ የብሔረሰብ አስተዳደር እርከን ከአንድ በላይ የብሄረሰብ ምክር ቤትና የብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ሊኖረዉ አይችልም፡፡

2 የዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር (1) ድንጋጌ ቢኖርም በጉሙዝ ብሄረሰብ የአስተዳደር እርከን ዉስጥ በመተከልና ካማሺ መካከል ያለዉ እርቀት ለአስተዳደር የማይመች በመሆኑ በአንደኛዉ ቅርንጫፍ የአስፈጻሚ አስተዳደር እና የዳኝነት አካል ሊኖረዉ ይችላል አፈጻጸሙ በራሱ ምክር ቤት የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 6. የምክር ቤቱ አጠቃላይ አደረጃጀት

1. የብሔረሰቡ ምክር ቤት አጠቃላይ አደረጃጀት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

   ሀ. የብሔረሰቡ ምክር ቤት አጠቃላይ ጉባኤ፣

   ለ. የአፈ ጉባኤና የብሔረሰቡ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት፣

   ሐ. የብሔረሰቡ ምክር ቤት ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች፣

   መ. በብሔረሰቡ ምክር ቤት ውስጥ መቀመጫ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲ ተጠሪዎች፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተዘረዘረው ቢኖርም የክልሉ ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች አካላትን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

## 6 የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ

የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ የየብሄረሰብ ምክር ቤቱ መደበኛና አስቸኳይ ጉባኤ ያሆናል

## 7 የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባራት

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት ለፌዴራል የሕዝብ ተወካዮችና ለፌደረሽን ምክር ቤት

በዚህ ሕገ-መንግስት ደግሞ ለክልሉ ምክር ቤት የተሰጣቸው ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤቶች የየብሔረሰባቸው የበላይ ፖለቲካ ስልጣን ባለበቶች ናቸው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ስር የሰፈረው አጠቃላይ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለክልል ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

ሀ/ የሚጠቀምበትን የስራ ቋንቋ ይወስናል፣

ለ/ ብሔረሰብ በቋንቋው ለመናገርና ለመጻፍ፣ ቋንቋውን ለማሳደግ፣ ለመጠበቅ፣ ለመግለጽ፣ ለማዳበርና ለማስፋፋት፣ እንዲሁም ታሪኩን በማንከባከብ ያለውን መብት ማስጠበቅ፣

ሐ/ በዚህ ሕገ-መንግስት ለክልሉ ምክር ቤት የተሰጠው የህግ አውጭነት ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በተደራጀበት አከባቢ በክልል አቀፍ ሕግጋት፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር በማይፃረር ሁኔታ የራሱን ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ አወጥቶ ሥራ ላይ ያውላል፣

መ/ የክልሉ ምክር ቤት ያጸደቀውን እቅድና በጀት መሠረት በማድረግ የአከባቢውን ዕቅድና በጀት መርምሮ ያጸድቃል፣

ሠ/ የምክር ቤቱን አፈ-ጉባዔ፣ ምክትል አፈ-ጉባዔና ዋና አስተዳዳሪውን መርጦ ይሰይማል፣

ረ/ በዋና አስተዳዳሪ የሚቀርቡለትን የብሔረሰብ አስተዳደሩን ምክትል አስተዳዳሪና ሌሎች የአስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት መርምሮ ያጸድቃል፣

ሰ/ በብሄረሰብ አስተዳደሩ ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ሹመት ላይ የበኩሉን አስተያየት ለክልል ምክር ቤት ይሰጣል፣

ሠ/ የብሔረሰብ አስተዳደሩን ዋና አስተዳዳሪ ጨምሮ ሌሎች የአስተዳደር ባለስልጣናትን ለጥያቄ ይጠራል፣ አሰራራቸውንም ይመረምራል፡፡

## 8 የምክር ቤቱ አባላት አመራረጥና ስብጥር

1. እያንዳንዱ የብሔረሰብ ምክር ቤት ለክልል ምክር ቤት አባልነት የተመረጡ የብሄረሰቡን ተወካዮች እና በውስጡ ከታቀፉት የወረዳ

ምክር ቤቶች በልዩ ሁኔታ የሚመረጡ አባላትን ይይዛል፡፡

2. ከላይ በንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚደራጁ ምክር ቤቶች የአባላት ቁጥር በእያንዳንዱ ብሄረሰብ የሚወሰን ሆኖ ከ 75 የማይበልጥ ይሆናል፡፡

3. ከላይ በንኡስ አንቀጽ (1 እና 2) የተመለከተዉ የምክር ቤቱ አባላት አመራረጥ የብሄረሰቡን ተቃዋሚ ፓርቲ(ዎች) ተሳትፎን የጠበቀ መሆን አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚመረጡ የምክር ቤቱ አባላት የክልል ወይም የወረዳ ምክር ቤት አባልነት ሲያጡ የብሄረሰብ ምክር ቤት አባልነትን ያጣሉ፡፡

5. ከላይ የንኡስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ዉጭ በሆኑ ምክኒያቶች የብሄረሰብ ምክር ቤት አባልነት ሊያጣ የሚችለዉ በክልሉ ምክር ቤት አባላት የስነምግባር ደንብ ቁጥር 22/1999 ለክልል ምክር ቤት አባላት ስለ ስነ ምግባር በተደነገገዉ መሰረት ሲሆን ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 9 ስለምክር ቤቱ አመራር

ምክር ቤቱ የራሱ ጽህፈት ቤት ኖሮት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የሚመረጡ የራሱ አፈ-ጉባዔና ምክትል አፈ-ጉባዔ ይኖረዋል፤እንደ አስፈላጊነቱ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን ሊያደራጅ ይችላል፡፡

## 10 ስለ አፈ-ጉባኤውና ምክትል አፈ-ጉባኤው አመራረጥ

1 በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 75 ንዑስ አንቀጽ 3(ሠ) መሠረት ምክር ቤቱን የሚመሩ አፈ-ጉባኤና ምክትል አፈ-ጉባኤ በምክር ቤቱ ይመረጣሉ፡፡

2 ለአፈ-ጉባኤነት እጩ ሆነው የሚቀርቡት ከ3 የማይበልጡ የምክር ቤት አባላት ይሆናሉ፡፡ እነርሱም የምክር ቤቱን ተሰብሳቢ አካላት 1/3ኛ የድምጽ ድጋፍ ያገኙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

3 የቀረቡት እጩዎች ከአንድ በላይ በሆኑ ጊዜ አፈ-ጉባኤውን ለመምረጥ እጅ በማውጣት ድምጽ ይሰጣል፣ አብላጫ ድምጽ ያገኘውም አፈ-ጉባኤ ይሆናል፡፡

4 የዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 3 ድንጋጌ ቢኖርም አንድ ተወዳዳሪ ብቻ በእጩነት በቀረበ ጊዜ አፈ-ጉባኤው በቀጥታ ድጋፍ (በአክላሜሽን) ይመረጣል፡፡

5 ከላይ የተዘረዘረው የአፈ-ጉባኤው የአመራረጥ ሥርዓት ለምክትል አፈ-ጉባኤውም በተመሣሣይነት ይፈፀማል፡፡

## 11 የአፈ-ጉባኤውና የምክትል አፈ-ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር

1. አፈ-ጉባኤው በተሻሻለው የክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 76(2)፣ 53፣ 54፣ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

ሀ. የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፣ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመቀናጀት ዕለታዊ አጀንዳዎችን ይቀርጻል፣ አስቀድሞም የምክር ቤቱ አባላት እንዲያውቁ ያደርጋል፡፡

ለ. ምክር ቤቱን በመወከል ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነቶችን ያደርጋል፣

ሐ. የምክር ቤቱን ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች፣ ፀሐፊዎችና አባላት፣ የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት ኃላፊ እንዲሁም ሌሎች በአፈ-ጉባኤው አቅራቢነት የሚሾሙ አካላትን አቅርቦ ያስመርጣል፣ ያሾማል፣

መ. የምክር ቤቱን ኮሚቴዎች ሥራዎችን ያስተባብራል፣

ሠ. የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት ያደራጃል፣ ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣

ረ. ምክር ቤቱ በአባሎች ላይ እንዲወሰድ የወሰነውን የዲስፒሊን እርምጃ ያስፈጽማል፣

ሰ. ከሥልጣኑና ተግባሩ ውስጥ በከፊል ለምክትል አፈ-ጉባኤው በጽሁፍ ሊሰጥ ይችላል፡፡

ሸ. በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

2. **የምክትል አፈ-ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር**

ምክትል አፈ-ጉባኤው ተጠሪነቱ ለአፈ-ጉባኤውና ለምክር ቤቱ ሆኖ በህገ-መንግሥቱና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

ሀ. አፈ-ጉባኤው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ወይም አቋም ይዞ በምክር ቤቱ ውይይት ለመሣተፍ በሚፈልግበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፡፡

ለ. በአፈ-ጉባኤው ወይም በምክር ቤቱ ተለይተው የሚሠጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

12 **የምክር ቤቱ ሥራ ዘመን፣ የሥራ ጊዜ፣ ምላዓተ-ጉባዔና የውሳኔ አሰጣጥ**

**ሥነ-ሥርዓት**

1. ምክር ቤቱ የሚከተሉት የስብሰባ ዓይነቶች አሉት፡-

ሀ/ መደበኛ ስብሰባ፣

ለ/ አስቸኳይ ስብሰባ፡፡

2. የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አምስት አመት ይሆናል። የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞ ምክር ቤት የስራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ስራውን ይጀምራል።

3. ምክር ቤቱ ቢያንስ በዓመት ሦስት ጊዜ ይሰበሰባል።

4. ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምላዓተ-ጉባዔ ይሆናል። የምክር ቤቱ ውሳኔ በስብሰባ ላይ ከተገኙት አባላት አብላጫ ድምጽ ይተላለፋል።

5. የምክር ቤቱ ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል። ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ-ጉባዔ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። የብሔረሰቡ ዋና አስተዳዳሪ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል 1/3ኛው የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ-ጉበዔው ምክር ቤቱን ለስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

## 13 ስለ ብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር

የብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር በህገ መንግስቱ አንቀጽ (78–83) በተደነገገዉ መሰረት ሲሆን ዝርዝር አደረጃጀቱን፣ ስልጣኑና ተግባራቱን በተመለከተ በክልሉ የአስፈጻሚ አካላት ማደራጃና ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ መሰረትና በመስተዳድር ምክር ቤቱ በሚወጣ ዝርዝር ደንብ የሚወሰን ይሆናል ።

## 14 ስለ ተጠሪነት

በክልሉ ህገ መንግስት የተጠሪነት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ በዚህ አዋጅ መሰረት በብሄረሰቡ የአስተዳደር እርከን ዉስጥ የሚገኝ የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ተጠሪነት ለብሄረሰቡ አስተዳደር ምክር ቤት እንዲሁም የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነት ለብሄረሰቡ አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪ ይሆናል ::

## 15 ስለብሄረሰብ አስተዳደር የዳኝነት አካል

1 የብሄረሰብ አስተዳደር እርከን የዳኝነት አካል መደበኛና ነጻ የዳኝነት አካል ሆኖ አሰራሩም በህገ መንግስቱ በሰፈሩ የዳኝነት ድንጋጌዎች፣በዳኞች ማቋቋሚያ አዋጅና በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት ይሆናል።

2 የብሄረሰብ አስተዳደር እርከን ከመደራጀቱ በፊት የነበረዉ የከፍተኛ ፍርድ ቤት

የዳኝነት ስልጣን በዚህ አዋጅ ለብሄረሰብ አስተዳደር የዳኝነት አካል ተላልፏል።

3 ከብሄረሰብ አስተዳደር ዉጭ ለሚተዳደሩ እና ከብሄረሰብ አስተዳደር ጋር እኩል የተጠሪነት ስልጣን ላላቸዉ የከተማ አስተዳደሮች የዳኝነት አካል በአዋጅ ቁጥር 69/1999 አንቀጽ 50 ከተሰጠዉ ከተማ ነክ ስልጣን ዉጪ የሆኑት ጉዳዮችን የሚዳኝ የክልሉ የዳኝነት አካል በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

## ክፍል ሶስት
## ስለ ምክር ቤቶቹ ጽህፈት ቤቶች

### 16 ስለምክር ቤቶቹ ጽ/ቤት ስልጣንና ተግባር

*በዚህ አዋጅና በአዋጅ ቁጥር 32/1995 አንቀጽ (4)መሰረት የተቋቋመዉ የየብሄረሰብ ምክር ቤት ጽህፈት ቤቶች የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት አላቸዉ፤*

1. ለምክር ቤቱና ለቋሚ አካላቱ የጽህፈት አገልግሎት ይሰጣል፣
2. ለምክር ቤቱና ቋሚ አካላቱ የመሰብሰቢያ አዳራሾችን ያዘጋጃል፣
3. የምክር ቤቱና ቋሚ አካላቱን ቃለ ጉባኤ፣ዉሳኔዎችና ሰነዶች ተመዝግበዉ እንዲያዙና እንዲጠበቁ ያደርጋል፣
4. ለምክር ቤቱና አካላቱ የቤተ መጽሀፍት፣የምርምርና የመረጃ አገልግሎት ይሰጣል፣
5. በምክር ቤቱ የሚወጡ መጽሄቶችና ጋዜጦች ያሳትማል ፣ያሰራጫል፣
6. የምክር ቤቱ እንግዶች አስፈላጊዉን የመስተንግዶ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፣
7. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ዉል ይዋዋላል፣ይከሳል፣ይከሰሳል፣
8. የምክር ቤቱንና የቋሚ አካላቱን ስራዎች ለመስራት የሚያስችሉ ሌሎች ተግባራትን ያከናዉናል ።

### 17 የጽህፈት ቤቶቹ ኃላፊዎች ስልጣንና ተግባር

1 እያንዳንዱ የብሄረሰብ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት አንድ ኃላፊና ሌሎች ሰራተኞች የሚኖሩት ሲሆን የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ የጽህፈት ቤቱን ስራዎች ይመራል ያስተዳድራል።

2 የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ሀ. ኃላፊዉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 መሰረት ለጽህፈት ቤቱ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ስራ ላይ ያዉላል፣

ለ. የጽህፈት ቤቱን ሰራተኞች በክልሉ መንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ህግ መሰረት ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፣

ሐ. የጽህፈት ቤቱን አመታዊ በጀትና የስራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለአፈ ጉባኤዉ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ስራ ላይ ያዉላል፣

መ. የጽህፈት ቤቱን ሂሳብ በፋይናንስ ህግና ደንብ መሰረት ያንቀሳቅሳል፣

ሠ. ከአፈ ጉባኤዉ በሚሰጠዉ አመራር መሰረት ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ጽህፈት ቤቱን ይወክላል፣

ረ. የጽህፈት ቤቱን እንቅስቃሴና የሂሳብ ሪፖርት ለአፈ ጉባኤዉ ያቀርባል፣

ሰ. ለስራ ቅልጥፍና ሲባል ከተግባሩ ከፊሉን በዉክልና ለጽህፈት ቤቱ ሰራተኖች ሊያስተላልፍ ይችላል፣ ሆኖም ዉክልናዉ ከአንድ ወር ለሚበልጥ ጊዜ ከሆነ አፈ ጉባኤዉ ማጽደቅ ይኖርበታል።

ሸ. ከአፈ ጉባኤ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል።

## 18 በጀት

የጽህፈት ቤቱ በጀት በብሄረሰቡ ምክር ቤት ይወሰናል።

## 19 የሂሳብ መዛግብት

1. ጽህፈት ቤቱ የተሟላ የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶች ይይዛል፤

2. የጽህፈት ቤቱ መዛግብትና ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር ይመረመራሉ

## ክፍል አራት
## የኮሚቴዎች ውስጣዊ አደረጃጀትና አሠራር

## 20 ስለ ምክር ቤቱ የተለያዩ ኮሚቴዎች

ምክር ቤቱ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 76(3) እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት የኮሚቴ ዓይነቶች ይኖሩታል።

1. ቋሚ ኮሚቴ
2. ንዑስ ኮሚቴ
3. ጊዜያዊ ኮሚቴ

## 21 የቋሚ ኮሚቴዎች ሥልጣንና ተግባር

የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች የሚከተሉት አጠቃላይ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል።

1. ህጉ በሚሰጠዉ የስልጣን ገደብ ዉስጥ መመሪያ ማመንጨት፣
2. በተመሩላቸው ረቂቅ መመሪያዎችና ዉሳኔዎች ላይ የበሰለ የውሣኔ ሃሣብና አስተያየት እያዘጋጁ ለምክር ቤቱ ያቀርባሉ፣
3. እንደየአግባቡ የተደለደሉላቸውን የአስተዳደሩን መንግሥታዊ አካላት አሠራር ይከታተላሉ፣ ይቆጣጠራሉ፣
4. ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ በተለያዩ መንገዶችና ሁኔታዎች የሚቀርቡላቸውን አቤቱታዎች እንደየአግባቡ ተቀብለው ያስተናግዳሉ፣

5. በተቋቋሙበት ዓላማ ዙሪያ ጥናት ያካሂዳሉ፣ ህጐች፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ኘሮግራሞች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላሉ፣

6. ልዩ ልዩ አውደ ጥናትና የውይይት መድረኮች ያዘጋጃሉ የልምድ ልውውጦችን ያደርጋሉ፣

7. ሥራቸውን በንዑሳን ኮሚቴዎች ተከፋፍለው ሊያከናውኑ ይችላሉ፣

8. መመሪያ በማውጣት ተግባርና የአስፈጻሚ አካላት ክትትል በሚደረግበት ወቅት ሂደቱ የጾታ አድልዎን ያስወገደና ሥርዓተ ጾታን ያገናዘበ መሆኑን ያረጋግጣሉ፣

9. በብሄረሰብ ምክር ቤቱ በኩል ለክልሉ ምክር ቤት የሚመነጩ የህግ ረቂቆችን ያዘጋጃሉ፣

10. ከመንግስታዊ ተግባራት በተጨማሪ ህገ መንግስታዊ የብሄረሰብ ነክ መብቶችን ለማስከበርና የክልሉ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች አንድነትን የበለጠ ለማጠናከር ከሌሎች አቻ የብሄረሰብ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች ጋር የልምድ ልዉዉጥ ያደርጋሉ፣

11. በምክር ቤቱ ወይም በአፈ-ጉባኤው የሚሰጣቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናሉ።

## 22 የቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀት

1. እያንዳንዱ ምክር ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ቋሚ ኮሚቴዎች ይኖሩታል፣

ሀ. የብሔረሰብ ነክ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣

ለ. የህግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣

ሐ. የኢኮኖሚ ፣የበጀትና የመንግስት ሂሳብ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣

መ. የአቅም ግንባታ፣ ማህበራዊ እና የሴቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣

2. ቋሚ ኮሚቴዎቹ ተጠሪነታቸው ለምክር ቤቱና ለአፈ-ጉባኤው ይሆናል።

3. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢውንና ፀሐፊውን ጨምሮ በአፈ-ጉባኤው አቅራቢነት በምክር ቤት የሚሰየሙ እስከ 5 የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል።

4. አንድ የምክር ቤት አባል በአንድ ጊዜ ከአንድ ቋሚ ኮሚቴ በላይ አባል ሆኖ ሊሠራ አይችልም።

5. አንድ የቋሚ ኮሚቴ አባል ኮሚቴው ከሚከታተለው የመንግስት አካላት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለው መሆን አለበት።

6. የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች ተጠሪነታቸው ለአፈ-ጉባኤውና ለየኮሚቴዎቻቸው ይሆናል፡፡

## 23 የብሔረሰብ ነክ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

1. የብሔረሰብ ነክ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ዋናው ዓላማ ብሔረሰቦች በሕገ-መንግስት ጥበቃ በተደረገላቸው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የባህልና የአከባቢ ልማቶች ውስጥ በስፋት በመሳተፍ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ምቹ ሁኔታ ማመቻቸት ሲሆን በተለይም፡-

   ሀ/ ከብሔረሰቦች መካከል የሚነሱት የጥቅም ግጭቶች መንስዔውችን ተከታትሎ በማጥናት ለችግሮቹ መፍቲሄ የሚሆን የዉሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ እና ለሚመለከተዉ አካል ያቀርባል፤

   ለ/ ብሔረሰቡ በሕገ-መንግስቱ የተረጋገጠለትን መሰረታዊ መብቶችና ጥቅሞች በአግባቡ ስለመጠቀሙና በሂደት ዙሪያ የሚያጋጥሙትን ጉዳዮች በመለየት ክትትል ያደርጋል፣ ለብሄረሰቡ መብት መከበርም ምክር ቤቱ የሚሰጠዉን ተግባር ይፈጽማል፣

   ሐ/ ብሔረሰቡ በቋንቋ ለመናገር፣ ለመፃፍ፣ ቋንቋውን ለማሳደግ፣ ለመጠበቅ ለመግለጽ፣ ለማዳበርና ለማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን ለማንከባከብ ያለውን መብቶች መከበራቸዉን ያረጋግጣል፣

   መ/ የክልሉ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መካከል በመግባባትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነትን የሚያጠናክሩ ተግባራትን ያከናዉናል፣ ከአቻ የብሄረሰብ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች ጋር የልምድ ልዉዉጦችን ያደርጋል፣ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣

2. የብሔረሰብነክ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሠረት ከብሔረሰብ ነክ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ መልኩ የሚነሱ ጥያቄዎች ሲነሱ የመፍቲሄ ሀሳብ ያቀርባል፣ የብሄረሰብ ነክ ጉዳዮችን የሚያከናዉኑ መሥሪያ ቤቶችን ይከታተላል፡፡

## 24 የሕግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

1. የሕግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ዋና ዓላማ የብሔረሰቡ አስተዳደር መንግሥት የፍትህና አስተዳደራዊ ሥርዓቶች ሕገ-መንግሥቱን መሠረት በማድረግ መደራጀታቸውንና መፈፀማቸውን ለመከታተል፣ እንዲሁም በዚህ በዘርፉ ያለውን መሠረታዊ ችግር በጥናት የሚታረምበትን አቅጣጫ መንደፍን ሲሆን በተለይም፡-

ሀ. ህብረተሰቡ በሕገ-መንግሥቱ የተረጋገጠለትን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸዉና በሂደት ዙሪያ የሚያጋጥሙትን ችግሮች በመለየት መፍቲሄ ማስገኘት፣

ለ. ሕዝብ ከተፅዕኖ ነጻ በሆነ የዳኝነት ሥርዓት በአግባቡ መገልገሉን፣

ሐ. ሕግ ነክ ፖሊሲዎች፣ እስትራቴጅዎች፣ ኘሮግራሞችና ስምምነቶች መነደፋቸውና መተግበራቸውን በተመለከተ ክትትልና ምርመራ ማድረግ ነው፡፡

2. የህግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉትን በብሔረሰብ አስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙትን መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች ይከታተላል፡፡

ሀ. የብሄረሰብ አስተዳደር የዳኝነት አካል (ከፍተኛ ፍርድ ቤት)፣

ለ የብሄረሰቡን አስተዳደር ምክር ቤት፣

ሐ. የፍትህ ጽ/ቤት፣

መ. የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት፣

ሠ. ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥር ‘መ’ ሥር ለተመለከተው ጽ/ቤቶች ተጠሪ የሆኑ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች፡፡

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ ሥር የተዘረዘሩትን አካላት በተመለከተ ተለይቶ የተሰጧቸውን ሥልጣንና ተግባር ስለመፈጸማቸዉ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይመረምራል፣ ሪፖርቱንም ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡

4. ከላይ በንዑስ ቁጥር 2/ሀ/ የተጠቀሰውን አካል በተመለከተ ኮሚቴዉ ክትትልና ቁትጥር የሚያደርገዉ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 66 ድንጋጌን መሠረት በማድረግና የዳኝነት ነጻነትን በማይጋፋ መልኩ የዳኝነቱን አስተዳደራዊ ስራዎችንና ህብረተሰቡ የቀልጣፋ አገልግሎት ተጠቃሚ ስለመሆኑ ይሆናል፡፡

**25 የኢኮኖሚ፣የበጀትና የመንግስት ሂሳብ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ**

1. የኢኮኖሚ፣የበጀትና የመንግስት ሂሳብ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ፡-

   ሀ. ኋላ ቀር የአስተራረስ ዘዴዎች ተለውጦ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ፣ በምግብ እህል ራስን የመቻልና የምግብ ዋስትና የማረጋገጥ አላማችን ግብ እንዲመታ እንዲሁም ግብርና መር የሆኑ የኢኮኖሚ ልማት እስትራቴጂዎችን ለማሳካት የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ኘሮግራሞች እቅዶች በተገቢው መንገድ መፈፀማቸውን መከታተልና መመርመር፣ እንዲሁም

   ለ. የሀገሪቱና የክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ፖሊሲ እና እስትራቴጂ በብሔረሰብ አስተዳደሩ ብሎም በክልሉን የኢኮኖሚ እድገት በሚያፋጥን መልኩ ተግባራዊ መሆኑን፣ ንግድና ኢንዱስትሪ እንዲሁም ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እንዲስፋፉ የሚያበረታቱ ተግባራት በአግባቡ መከናወናቸውን፣ የኢንቨስትመንት ፖሊሲና ህግ በመስኩ ለሚሠማሩ ምቹ ሁኔታዎች መፈጠራቸውን ማረጋገጥ ይሆናል ፡፡

   ሐ. የብሔረሰብ አስተዳደሩ መንግሥቱን ዓመታዊና ተጨማሪ በጀት፣ እንዲሁም የኦዲት ውጤቶችና መንግሥታዊ የሆነው ገንዘብና ንብረት መሰብሰቡን፣ መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን በክልሉ ፖሊሲዎችና ህጐች መሠረት መከታተልና መቆጣጠር ነው፡፡

   መ. የብሄረሰብ አስተዳደሩን አመታዊና ተጨማሪ የበጀት ረቂቅን ዝርዝር ይመረምራል፣ የውሣኔ ሃሣቡን በማከል ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡

2. የኢኮኖሚ፣የበጀትና የመንግስት ሂሳብ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሚከተሉትን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ይከታተላል፡-

   ሀ. ግብርናና ገጠር ልማት ጽህፈት ቤት፣

   ለ. ንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርትና ኢንቨስትመንት ጽህፈት ቤት፣

ሐ. የውኃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ጽህፈት ቤት፣

መ. ሥራና ከተማ ልማት ጽህፈት ቤት፣

ሠ.የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት፣

ረ. የገቢዎች ጽህፈት ቤት።

ሰ ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥሮች (ሀ- ረ) ሥር ለተጠቀሱት መስሪያ ቤቶች ተጠሪ የሆኑና የሚሆኑ መሥሪያ ቤቶች ይከታተላል፣ይቆጣጠራል።

3 ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ ሥር የተዘረዘሩትን አካላት በተመለከተ በማናቸውም በተሰጧቸው ሥልጣንና ተግባር ዙሪያ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይመረምራል።

## 26 የአቅም ግንባታ፣ ማህበራዊና የሴቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

1. የአቅም ግንባታ፣ ማህበራዊና የሴቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ፡-

ሀ. በብሔረሰብ አስተዳደሩ ብሎም በክልሉ ውስጥ ፈጣን ልማትን ለማምጣትና በዴሞክራሲ የታነፀ ህብረተሰብን ለመፍጠር በብቃት፣ በጥራት፣ በታማኝነትና በቁርጠኝነት ሊሠራ የሚችል የሰለጠነ የሰው ኃይል በአጭር ጊዜና በሰፊው ማፍራት፣

ለ. የብሔረሰብ አስተዳደሩን ብሎም የክልሉን አጠቃላይ የማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ የትምህርትና የጤና ነክ አገልግሎት ማስፋፋትና የጤና ጠንቆችን ማስወገድ፣

ሐ. የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ስርጭትን ለመግታት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን፣ የማህበራዊ ዋስትና አልግሎቶችን፣ የአረጋዊያንና የአካል ጉዳተኞች ድጋፍ እንክብካቤ፣ የህጻናት ደህንነት ጥበቃ የሥራ አጥነትና እየተከታተለ፣ እያጠናና እየገመገመ አስተያየትና የውሳኔ ሃሣቦች ለምክር ቤቱ ማቅረብ ነው።

መ. ሴቶችን የሚጨቁኑ ህጐችን መመርመርና እንዲሻሻሉ ማድግና

አዳዲስ የሕግ ሐሣቦችን ማመንጨት ለሚመለከተዉ አካል ማቅረብ፣

ሠ. አዋጆችና ዕቅዶች ሲወጡም ሆነ ሲፀድቁ የጾታ አድሎን ያስወገዱና ስርዓተ ጾታን ያገናዘቡ እንዲሆኑ የበኩላቸዉን አስተያየት ለክልል ምክር ቤትና ለሚመለከተዉ አካል መስጠት፣

ረ. በፖለቲካ፣በኢኮኖሚያዊና በማህበራዊ መስኮች እንዲሁም በመንግሥትና በግል ተቋማት ሴቶች ከወንዶች እኩል ተወዳዳሪና ተሣታፊ እንዲሆኑ ለማስቻል፣ በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃ /ትኩረት/ እንዲጠቀሙ ማስደረግ፣

ሰ. ሴቶች ያሏቸውን ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደርና የመቆጣጠር፣ የመጠቀም፣ የማስተላለፍና የመውረስ መብቶቻቸውን ማስከር፣

ሸ. ሴቶች ያላቸው በቅጥርና በደረጃ እድገት እንዲሁም የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ መብት እንዲከበር ማድረግ፣

ቀ. ከጐጂ ልማዳዊ ባህል ተፅዕኖ ይላቀቁ ዘንድ ሴቶችን የሚጨቁኑና በአካላቸው ወይንም በአእምሮዋቸው ላይ ጉዳት የሚያደርሱትን ወጐችና ልምዶችን መከላከል፣

በ. በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርትና የመረጃ አቅም የማግኘት መብታቸውን ማስከበር፣

ተ. በጥያቄዎቻቸው ዙሪያ እንደፍላጐታቸውና እንደ ችግራቸው ዓይነት ተደራጅተው ሊታገሉ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይሆናል፡፡

2. የአቅም ግንባታ፣ማህበራዊና የሴቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሚከተሉትን ይከታተላል፣

ሀ. የአቅም ግንባታ ጽህፈት ቤት፣

ለ. የማስታወቂያ፣ ባህል፣ ቱሪዝምና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት፣

ሐ. የጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት፣

መ. የትምህርት ጽህፈት ቤት፣

ሠ. የወጣቶች ስፖርት ጉዳይ ጽህፈት ቤት፣

ረ. የሴቶች ጉዳይ ጽህፈት ቤት፣

ሰ. ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥር ሀ--ሰ ለተጠቀሱት መስሪያ ቤቶች ተጠሪ የሆኑት መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች፣

3 በዚህ አዋጅ መሠረት ከሥርዓተ-ጾታ ጋር ጥያቄ የሚያስነሱ ማናቸውም መሥሪያ ቤቶችን ይከታተላል፡፡

3. ከላይ በተጠቀሰው ንዑስ አንቀጽ /2/ የተዘረዘሩትን አካላት በተመለከተ በማናቸውም በተሰጧቸው ስልጣንና ተግባራት ዙሪያ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይመረምራል፡፡

27 **የቋሚ ሚቴዎች አመራሮች ሥልጣንና ተግባር**

1. የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

ሀ. ቋሚ ኮሚቴዎቹን በመወከል ከሌሎች ወገኖች ጋር ግንኙነት ያደርጋሉ፣

ለ. እንደየሥራ ዘርፋቸው ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባሉ፣

ሐ. ኮሚቴዎቻቸውን ይመራሉ፣ ያስተባብራሉ፣ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓትንም ያስጠብቃሉ፣

መ. ተጋባዥ እንግዶች እንዲገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፣

ሠ. በምክር ቤቱ፣ በአፈ-ጉባኤውና በኮሚቴው የሚሰጧቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናሉ፡፡

2. የቋሚ ኮሚቴዎች ፀሐፊዎች በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፣

ሀ. ሰብሳቢዎቹ በማይገኙበት ጊዜ ተክተው ይሠራሉ፣

ለ. የኮሚቴዎቹ ሠነዶችና ቃለ-ጉባኤዎች በአግባቡ መያዛቸውንና

መቀመጣቸውን ያረጋግጣሉ፣

ሐ. በኮሚቴዎቻቸውና በሰብሳቢዎቻቸው የሚሰጧቸውን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናሉ፡፡

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ሥር የተገለፁት አመራሮች የሥራ እንቅስቃሴያቸውን በየኮሚቴዎቻቸው አባሎች እውቅና የመምራት ግዴታ አለባቸው፡፡

## 28 የኮሚቴዎችን ሪፖርት ስለማዳመጥ

1. የምክር ቤቱ ኮሚቴዎች አፈ-ጉባኤው በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በተሰጣቸው ተግባር ዙሪያ በአመራሮቻቸው ወይም በተወካዮቻቸው አማካኝነት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባሉ፣
2. ኮሚቴዎች የሚያቀርቡት ሪፖርት፣

   ሀ. ወቅታዊ አጠቃላይ የሥራ አፈጻጸምና፣

   ለ. በየጊዜው በምክር ቤቱ እና በአፈ-ጉባኤው የሚመሩላቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ይሆናል፣
3. የምክር ቤቱ አባላት ኮሚቴዎቹ ባቀረቡት ሪፖርት ዙሪያ ውይይት ያደርጋሉ፣ አስተያየት ይሰጣሉ እንደነገሩ ሁኔታ ውሳኔዎችን ሊያሳልፉ ይችላሉ፣

## 29 የቋሚ ኮሚቴዎች አጠቃላይ አሠራር

የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች የሚከተሉት ዋና ዋና የአሠራር ሥልቶችና ሥነ-ሥርዓቶች ይኖሯቸዋል፡፡

1. በአፈ-ጉባኤውና በምክር ቤቱ የተመሩላቸውን ረቂቅ የዉሳኔ ሀሳቦች እንደየሁኔታው፣

   ሀ. ማስታወቂያ በማውጣት፣

   ለ. አስረጂዎችንና ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸውን አካላት በመጋበዝ፣

   ሐ. የህዝብ አስተያየት መስጫ መድረኮችን በማዘጋጀት ሪፖርትና የውሳኔ ሃሣብ ለምክር ቤቱ ያቀርባሉ፡፡
2. ቋሚ ኮሚቴዎች የመመርመርና የመከታተል ሥራዎችን የሚያከናውኑት የሚከተሉት ሥልቶችን በመጠቀም ነው፡፡

   ሀ. ከሚመለከቷቸው መሥሪያ ቤቶች እቅዶችንና የክንውን ሪፖርቶችን በመቀበል፣

ለ. ስብሰባዎችንና ኮንፈረንሶችን በመሣተፍ፣

ሐ. የሚመለከታቸውን አካላት ጠርተው በማነጋገር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙትም መግለጫ እንዲሰጡ በማድረግ፣

መ. ለሥራው አጋዥ የሆኑ የተለያዩ ጉብኝት በማድረግ፣

ሠ. ከተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች የሚደርሷቸውን ጥቆማዎችና አቤቱታዎች መነሻ በማድረግ፣

ረ. ከሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች ወይም አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር፣

ሰ. ሪፖርት በማዘጋጀት ወይም መግለጫዎችን በመስጠት፣

4. በአመታዊ እቅድ በመምራት እና አጠቃላይ አሠራራቸውን በመገምገም እና የህዝብ አስተያየትን በመሰብሰብ፣

5. ከላይ ከአንቀጽ 20–24 የቋሚ ኮሚቴዎች የሚመረምሯቸዉና የሚከታተሏቸዉ በብሄረሰብ አስተዳደር አካላት የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሲያሜ መለዋወጥ የቋሚ ኮሚቴ ስራ ላይ ተጽእኖ አይኖረዉም።

## 30 የቋሚ ኮሚቴዎች የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

1. ከቋሚ ኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፣

2. የቋሚ ኮሚቴው ውሳኔዎች በምልዓተ-ጉባኤው በአብላጫ ድምጽ ይተላለፋሉ፤ ሆኖም ድምፁ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፣

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ሥር የተመለከተው እንዲሁም የኮሚቴዎች የስብሰባ አካሄድና የውሳኔ አሰጣጥ ሁኔታ የምክር ቤቱን የአሠራር ሥነ ሥርዓት የሚከተል ሆኖ በዝርዝሩ መመሪያ ይወሰናል።

## 31 የቋሚ ኮሚቴዎች አባላት መብቶችና ግዴታዎች

1. የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች አባላት ከእለት ተእለት የኮሚቴ ሥራዎቻቸው ጋር የተያያዘ መልኩ የዉሎ አበልና የትራንስፖርት ክፍያ የማግኘት መብቶች ይኖሯቸዋል።

2. የቋሚ ኮሚቴዎች አባላት የሚከተሉት ዋና ዋና ግዴታዎች ይኖሩባቸዋል።

ሀ. በበቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በማናቸውም የኮሚቴ ስብሰባዎች የመገኘት፣

ለ. የተመደቡላቸውን ሥራዎች በአግባቡ የመከታተልና የመቆጣጠር፣

ሐ. በብሄረሰብ አስተዳደር ውስጥም ሆነ በክልሉ የሚደረጉ ጥናቶች፣ ስብሰባዎችና ሌሎች የመስክ ሥራዎች በሚወከል አባል በኩል ስለ ሁኔታው የተጠናከረ ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካል በየወቅቱ የማቅረብ፣

3. እያንዳንዱ የኮሚቴ አባል በተናጠልም ሆነ በጋራ ለሚያከናውነው ተግባር ኃላፊነት አለበት፤ ግዴታውን የማይወጣ ማንኛውም የኮሚቴ አባል በኮሚቴው አብላጫ ድምጽ ተገምግሞ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ይቀርብበታል። በክልል ምክር ቤት የአሰራር ደንብ መሰረት የእርምት እርምጃ ይወሰድበታል።

## 32 የንዑሳን ኮሚቴዎች አደረጃጀት፣ ስልጣን፣ ተግባርና አሠራር

1. ንዑስ ኮሚቴ ማንኛውም ቋሚ ኮሚቴ ኃላፊነቱን በብቃት ለመወጣት ሲባል የራሱን አባላት አመቺ በሆነ መልኩ በመከፋፈል የሚያደራጀው አካል ነው።
2. በቋሚ ኮሚቴው አባላት የሚመረጡ ማናቸውም ንዑስ ኮሚቴዎች የየራሳቸው ሰብሳቢና ፀሐፊ ይኖራቸዋል።
3. ንዑሳን ኮሚቴዎች በቋሚ ኮሚቴው ዓመታዊ የሥራ እቅድ ላይ በመመርኮዝ የየራሣቸው የሥራ እቅድ ያዘጋጃሉ፣ ይፈጽማሉ፣ ለቋሚ ኮሚቴው ሪፖርት ያቀርባሉ፣ በቋሚ ኮሚቴው የሚሰጣቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናሉ።

## 33 የጊዜያዊ ኮሚቴ አደረጃጀት፣ ሥልጣን፣ ተግባርና አሠራር

1. ምክር ቤቱ በቋሚ ኮሚቴዎች በቀጥታ ሊከናወኑ የማይችሉ አስቸኳይና አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸው ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል።
2. የጊዜያዊ ኮሚቴ ስልጣን በሚከሰተው አስቸኳይና አስፈላጊ ጉዳይ ዙሪያ ሆኖ ተልዕኮውን ለማከናወን አጠቃላይ የአሠራር አቅጣጫ በምክር ቤቱ የሚሰጠው ይሆናል።
3. የጊዜያዊ ኮሚቴ አባላት ብዛት እንደአስፈላጊነቱ በምክር ቤቱ

የሚወሰን ሆኖ፣ ኮሚቴውን የሚመሩ ሰብሳቢና ፀኃፊ ምክር ቤቱ ይመድብለታል፡፡

4. ማንኛውም ጊዜያዊ ኮሚቴ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ዙሪያ ሥራውን አጠናቆ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ካቀረበ በኂላ የሚከስም ይሆናል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 4 ላይ የተደነገገው ቢኖርም ምክር ቤቱ ሪፖርቱን አዳምጦ ቀሪ ሥራ መኖሩ ካረጋገጠ ሥራው እስኪጠናቀቅ ድረስ ጊዜያዊ ኮሚቴው የመሥራት ኃላፊነት አለበት፡፡

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

34 የብሄረሰቦች አለመግባባቶችን ስለሚፈታ አካል

በክልሉ ብሄር ብሄረሰቦች መካከል አለመግባባቶች ሲፈጠሩ የሚፈታ ከየብሄረሰቡ ምክር ቤቱ የተዉጣጣ እኩል ዉክልና ያለዉ ክልል አቀፍ አካል በዚህ አዋጅ የተቋቋመ ሲሆን ዝርዝሩ በሌላ ህግ ይወሰናል፡፡

35 ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጐች

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተካተቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

36 ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የክልሉ ምክር ቤት በማናቸዉም ሁኔታ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2. ምክር ቤቱ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

37 አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ጸድቆ በልሳነ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አሶሳ የካቲት 2000ዓ/ም

ያረጋል አይሸሽም ብረሄነ
የቤ/ጉ/ክ/መንግስት ኘሬዚዴንት